# ሥራ ፈት ምሁራን ከዘብጥያ?

ከድሚልኝ ብዕሬ - ዘአዲሱ ገበያ

የሠላም አምባ
አንጋፋ አዛውንት፣
በወህኒ ኑሮ
ከአይጥ ይሚገት?

በዓለም አቀፍ መድረክ
እንባ ጠባቂ፣
ለዘብጥያው ጎራ
ድመት ናፋቂ?

ወጣት ብልህ አኩሪ
ጠንካራ ሴት ዳኛ፣
ሕግን አክባሪ
የሰዉ ሞገደኛ?

ኢኮኖሚስቶች ኢንጅነሮቹ
ዜና ዘጋቢያን አርታዮቹ፣
ወህኒ አፍቃሪ ታዳሚዎቹ
ምክር አልሰሜ ቁንጮዎቹ?

ወይ ምሁሩ
ወይ መምህሩ፣
ይባስ ብሎ
የደቀ መዝሙሩ::
ዕዉቀትን ችላ ባይ፣
ዘብጥያን አማላይ::

ደግሞ ትምህርት ቤት
ለጥበብ ለዕዉቀት፣
ደግሞ ዩኒቨርስቲ
ኮሌጅን መገንባት፣
ሃ! ወህኒ ማን ሊያሞቅሽ
እንዴት ሊሰነበት?

የዕዉቀት ቤትና
ወህኒ ተወዳድረው፣
ወህኒ አሸነፈ
ዕዉቀትን ዘረረዉ::

ትምህርት አትማሩ
ዕዉቀት ምን ያደርጋል?
ምሁር ሁሉ አዳሩ
ዘብጥያዉ ታምቋል::

ዘብጥያ ዘብጥያ
ዘብጥያ ያማራችሁ፣
በሉ በርቱ እንግዲህ
ትምህርቱ ይቅናችሁ!
በርቺ በጣም በጣም
ኢትዮጵያ ሃገሬ፣
ቀለም የሚቆጥር
ደመኛ ነው ዛሬ::

ወህኒውን አስፍተሽ
ኮሌጁን አፍርሽው፣
አገር ለመገንባት
ምሁሩን ቀፍድጅው::

ሃይ ምሁር ሃይ ምሁር
ስንት ምሁር አለ፣
ጥቂት ለራስ አድሮ
ብዙው ለሰዉ አለ::

ለሰዉ የሆናችሁ
ለአገር ያሰባችሁ፣
ቁጥራችሁ በዛና
ወህኒ አጣበባችሁ፣
ይበላችሁ እንጂ
ደግሞ ሊያዝኑላችሁ!

ኸረ ወህኒ ሞላህ
አይበቃም ወዳጄ፣
ይሉኝታን ትዝብትን
ተማር ባክህ ልጄ::

ሥራ ፈተው ዛሬ
ሥራ ሰጥተውሃል፣
ፈተህ ጉድ ሥራቸው
ሳንተም ይበጅሃል::

© ድሚልኝ ብዕሬ - ዘአዲሱ ገበያ
zeaddisu_gebeya@yahoo.com
April 2006